مصادرنا في تلقي العقيدة

የዓቂዳ ምንጮቻችን



إعداد: الشيخ صالح بن فوزان الفوزان

ትርጉም፡ አቡ፣ ዓብዲልዓዚዝ/ ዩሱፍ አህመድ



ምስጋና ለዓለማት ጌታ የተገባው ነው። ውዳሴና ሰላምታ በነብያችን ሙሐመድ ፣ በቤተሰቦቻቸው እና በአጠቃላይ በባልደረቦቻቸው ላይ ይስፈን።

ከዚህ በመቀጠል፡

ዓቂዳ (እምነት) ለተግባራችን መሰረት ነው። ማንኛውም ማህበረሰብ እና ቡድን የራሱ የሆነ ዓቂዳ (እምነት) አለው። ትክክለኛ ወይም የተሳሳተ ዓቂዳ (እምነት) ሊሆን ይችላል። እምነቱ ጤናማና የተስተካከለ ከሆነ ተግባራቶች ሁሉ ጤናማና የተስተካከሉ ይሆናሉ። ምክንያቱም በሐቅ ላይ የተመሰረተ ፣ ሐቅ መሆኑ የሚያጠራጥር አይደለም። እምነቱ የተበላሸ ከሆነ ደግሞ ተግባራቱ ሁሉ ይበላሻል። ምክንያቱም በተበላሸ ነገር የተገነባ ሁሉ ብልሹ መሆኑ የማይቀር ነው።

ረሡል ﷺ ለህዝባቸው መጀመሪያ ጥሪ ያደረጉት ወደትክክለኛ ዓቂዳ (እምነት) ነው። ዓቂዳቸው (እምነታቸው) ከተስተካከለ የዒባዳ (የአምለኮ) ዘርፎችን ያስተምራሉ ፣ በእርሳቸው ላይ የወረደውን ሸሪዓዊ ህግ ቀስ በቀስ ያስተላልፋሉ።

አላህ በተከበረው ቁርኣናዊ አንቀጽ የሚከተለውን ተናግሯል፡-

﴿وَلَقَدْ بَعَثْنَا فِي كُلِّ أُمَّةٍ رَّسُولاً أَنِ اعْبُدُواْ اللّهَ وَاجْتَنِبُواْ الطَّاغُوتَ فَمِنْهُم مَّنْ هَدَى اللّهُ وَمِنْهُم مَّنْ حَقَّتْ عَلَيْهِ الضَّلالَةُ فَسِيرُواْ فِي الأَرْضِ فَانظُرُواْ كَيْفَ كَانَ عَاقِبَةُ الْمُكَذِّبِينَ﴾

"በየህዝቡም ሁሉ ውስጥ "አላህን ተገዙ፤ ጣዖትንም ራቁ" በማለት መልክተኛን በእርግጥ ልከናል። ከእነርሱም ውስጥ አላህ ያቀናው ሰው አለ። ከእነሱም

ውስጥ በእርሱ ካይ ጥመት የተረጋገጠበት ሰው አልከ። በምድርም ካይ ሂዱ ፤ የአስተባባዮችም መጨረሻ እንደት እንደነበረ ተመልከቱ።" (አን'ነሕል፡ 36)

﴿وَمَا أَرْسَلْنَا مِن قَبْلِكَ مِن رَّسُولٍ إِلَّا نُوحِي إِلَيْهِ أَنَّهُ لَا إِلَهَ إِلَّا أَنَا فَاعْبُدُونِ﴾

"ከአንተ በፊትም እነሆ ከእኔ ሌላ አምላክ የለምና ተገዙኝ በሚለት ወደርሱ የምናወርድለት ቢሆን እንጅ ከመልክተኛ አንድንም አልላክንም።" (አል'አንቢያ፡ 25)

﴿وَمَا أُمِرُوا إِلَّا لِيَعْبُدُوا اللَّهَ مُخْلِصِينَ لَهُ الدِّينَ حُنَفَاء وَيُقِيمُوا الصَّلَاةَ وَيُؤْتُوا الزَّكَاةَ وَذَلِكَ دِينُ الْقَيِّمَةِ﴾

"አካሀን ሃይማኖትን ከእርሱ ብቻ አጥሪዎች ፣ ቀጥተኛች ሆነው ኪግገዙት ፣ ሶላትንም አስተካክለው ኪሰግዱ ዘካንም ኪሰጡ እንጅ ያልታዘዙ ሲሆኑ (ተለያዩ)። ይህ የቀጥተኛይቱ (ሃይማኖት) ድንጋጌ ነው።" (አል'በይናህ፡ 5)

ሁሉም መልእክተኞች የሚከተለውን ጥሪ ለህዝቦቻቸው አስተላልፈዋል፡-

﴿يَا قَوْمِ اعْبُدُواْ اللَّهَ مَا لَكُم مِّنْ إِلَهٍ غَيْرُهُ﴾

"ወገኖቼ ሆይ! አካሀን ተገዙ። ከእናንተ ከርሱ ሌላ ምንም አምላክ የላችሁም።"
(አል'አዕራፍ፡ 59)

ሩሡሎች ዓቂዳን በማስተካከል ከህዝባቸው ጋር ለበርካታ ዘመናት አብረው ኖረዋል። መጀመሪያ ትኩረት ሰጠው መሰረቱን ይገነባሉ ፤ መሰረቱ ከተገነባ ፣ ዓቂዳ ከተስተካከለ በኋላ ሌሎችን የሸሪዓ ህግጋቶች ያዝዛሉ።

ነብዩ ሙሐመድ ﷺ የሩሡሎች ሁሉ መቋጫ ናቸው። ከእርሳቸው በኋላ ሌላ መልእክተኛ አይመጣም። ከዚህ በፊት ያለፉ ወንድሞቻቸው ባለፉበት ጎዳና አልፈዋል። በቅድሚያ ለህዝባቸው ጥሪ ያደረጉት ዓቂዳን እንዲያስተካክሉ ነው። ሽርክን እየከለከሉ ፣ ተውሒድን እያዘዙ አስራ ሶስት አመት መካ ተቀምጠዋል። ከዚያ በኋላ በሶላት ፣

በዘካ ፣ በጾም እና በሐጅ አዘዋል። ከዚያም ዲኑ ቀጥ እስኪልና እስኪሟላ በአላህ መንገድ ታግለዋል። የሙሽሪኮችን ጣዖት አፈራርሰው ፣ ጥርት ያለው ተውሒድ እንዲመሰረት አድርገዋል።

ረሡል ﷺ ለሙዓዝ ﷺ የሚከተለውን መልክት አስይዘው ወደየመን ልከዋል፡-

"إنك ستأتي قوما أهل كتاب ، فإذا جئتهم فادعهم إلى أن يشهدوا أن لا إله إلا الله ، وأن محمدا رسول الله ، فإن هم أطاعوا لك بذلك فأخبرهم أن الله قد فرض عليهم خمس صلوات في كل يوم وليلة ، فإن هم أطاعوا لك بذلك فأخبرهم أن الله قد فرض عليهم صدقة تؤخذ من أغنيائهم فترد على فقرائهم"

"ወደመጽሐፍ ባለቤቶች ትሄዳለህ ፣ ከዚያ በደረስክ ጊዜ ከአላህ በቀር በእውነት የሚመለክ አምላክ የሌለ መሆኑን መሀመድ የአላህ መልእክተኛ መሆናቸውን አንዲመሰክሩ ጥሪ አድርግላቸው። በዚህም ከታዘዙህ በቀንና በሌሊት አምስት ወቅት ሶላት አላህ ግዴታ ያደረገባቸው መሆኑን ንገራቸው ፤ በዚህም ከታዘዙህ ከሀብታሞች ተወስዶ ወደድሆች የሚመለስ የዘካ ግዴታ አንደለባቸው ንገራቸው።" (ቡኻሪ፡ 1496, ሙስሊም፡ 19)

መጀመሪያ ያዘዟቸው ከአላህ በቀር በእውነት የሚመለክ የሌለ መሆኑን ፣ መሀመድም የአላህ መልእክተኛ መሆናቸውን በእርግጠኛነት እንዲመሰክሩ ነው። ከዚያ በኋላ በሶላት ፣ በዘካ ነው ያዘዟቸው። ይህ የሚያስረዳው ዓቂዳ ተበላሽቶ ሶላትና ዘካ ፋይዳ ሊኖራቸው እንደማይችል ነው።

በዚሁ ጎዳና ላይ የረሡል ﷺ ምክትሎች እና የኢስላም መሪዎች ሁሉ ተጉዘዋል። ሁሉም ለትክክለኛው ዓቂዳ ትኩረት ሰጠዋል። እርሷን እንዲያስተካክሏት ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል።

በእርሷ ብርሃን ላይ ሰዎችን ወደአላህ ጥሪ አድርገዋል። መሰረቷን በትክክለኛ ዓቂዳ ላይ ያላደረገች ዳዕዋ ፍሬ አልባ ዳዕዋ እንደሆነች ግልጽ አድርገዋል።

ሁሉም ሰው በእርሷ የሚያምንባት የተለያየ ዓቂዳ (እምነት) አለው። ዓቂዳዎች ሁሉ የተገነቡበት መሰረቶች አሉት። መሰረቶች የተበላሹ ወይም ትክክለኛ ሊሆኑ ይችላሉ። አጋሪዎችና መቃብር አምላኪዎች ዓቂዳቸውን የመሰረቱት በጭፍን ተከታይነት ነው። አላህ በተከበረው ቁርኣናዊ አንቀጽ የሚከተለውን ተናግሯል፡-

﴿إِنَّا وَجَدْنَا آبَاءنَا عَلَى أُمَّةٍ وَإِنَّا عَلَى آثَارِهِم مُّقْتَدُونَ﴾

"እኛ አባቶቻችንን በሀይማኖት ላይ አገኘን ፤ እኛም በፈለጎቻቸው ላይ ተከታዮች ነን ያሉ ቢሆኑ እንጅ።" *(አዝ-ዙኽሩፍ፡ 23)*

﴿وَإِذَا قِيلَ لَهُمْ تَعَالَوْاْ إِلَى مَا أَنزَلَ اللهُ وَإِلَى الرَّسُولِ قَالُواْ حَسْبُنَا مَا وَجَدْنَا عَلَيْهِ آبَاءنَا أَوَلَوْ كَانَ آبَاؤُهُمْ لاَ يَعْلَمُونَ شَيْئًا وَلاَ يَهْتَدُونَ﴾

"ከእነርሱም አላህ ወደ አወረደውና ወደመልእክተኛው ኑ በተባሉ ጊዜ "አባቶቻችንን በርሱ ላይ ያገኘንበት ነገር ይበቃናል" ይላሉ። አባቶቻቸው ምንም የሚያውቁና የሚይመሩ ቢሆኑም (ይህንን ሚለት ይበቃቸዋልን?)" *(አል'ማኢዳህ፡ 104)*

የመቃብር አምላኪዎችና ከነርሱ የቀደሙት ሙሽሪኮች ዓቂዳ (እምነት) የተመሰረተው በጭፍን ተከታይነት ፣ በውሸት ቂሷዎች (ታሪኮች) እና በህልም ላይ ነው።

ሸይኹል ኢስላም ብን ተይሚያ ﷺ በሀመውያና በሌሎች ኪታቦቻቸው መግቢያ ላይ የጀህምያ ዓቂዳ (እምነት) የተያዘው ከአይሁዶች እንደሆነ ገለጸዋል።

የሙዕተዚላ ፣ የዓሻዒራ ፣ የማቱሪዲያ ዓቂዳ (እምነት) መሰረቱ ደግሞ ከፍልስፍና ፣ ከእርስ በርስ ክርክር እንዲሁም ከሎጅክ እንደሆነ ዑለሞች ገልጸዋል። (የአላህን ባህሪያት አስመልክቶ) "ጀውሐር" (የነገሮች ዋና ክፍል) ፣ "ጅስም" (አካል) ፣ "ዓረድ" (ባህሪ) እና የመሳሰሉ የክርክር መሰረታዊ ሐሳቦችን አንስተዋል።

የአህለሱና ወልጀማዓ ዓቂዳ (እምነት) መሰረት ቁርኣን ፣ ሐዲስ ፣ የሙስሊሞች ስምምነት እና የዚህ ኡመት መጀመሪያ የሆኑት ደጋገግ ቀደምቶች የነበሩበት ጎዳና ነው። ይህ ነው የአህለሱና ወልጀማዓ ዓቂዳ (እምነት)። የአህለሱና ወልጀማዓህ ዓቂዳ ጉድለት የሌለበት በሆነ ትክክለኛ መሰረት ላይ ነው የተገነባው። እርሱም የአላህ ኪታብ ፣ የረሡል ﷺ ሱና ፣ የዚህ ኡመት ቀደምቶችና አዒማዎች የነበሩበት ጎዳና ነው።

ቁርኣን፣ ዓቂዳን በማብራራት ፣ ምንም ተጋሪ የሌለውን አላህን በብቸኝነት እንድንገዛው ፣ ከአላህ ውጭ የሚመለኩ ነገሮች ደግሞ ሙሉ በሙሉ እንድንርቅ በሚያዙ መልእክቶች የተሞላ ነው። ቁርኣን በአላህ መልካም ስሞችና መገለጫዎች የተሞላ ነው። ቁርኣን የተሟሉ የሆኑ የአላህን ባህሪዎች በማጽደቅ ፣ ጎዶሎ እና ነውር ባህሪያትን ከአላህ ላይ በማጥራት የተሞላ ነው። ከላይ የጠቀስናቸው መልእክቶች በቁርኣን ውስጥ እንደተገኙት ሁሉ በነብዩ ﷺ ሐዲስም ተሟልተው ይገኛሉ።

ዓቂዳችን በአላህ ኪታብ ፣ በረሡል ﷺ ሱና የተመሰረተ ነው። አህለሱና ወልጀማዓዎች ሙዓጢላዎች የአላህን ስምና መገለጫዎች በሚያራቁቱ ሙዓጢላዎች ፤ የአላህን ባህሪያት ከፍጡር ጋር በሚያመሳስሉ ሙሽቢሃዎች ተቃራኒ አላህ ለነፍሱ ረሡል ﷺ ደግሞ ለአላህ ከስምም ይሁን ከመገለጫ ያጸደቁትን ያጸድቃሉ። አላህ ከነፍሱ ላይ ረሡል ﷺ ደግሞ ከአላህ ላይ ያጸዱትን ጎዶሎ ባህሪያት ያጸዳሉ።

አላህ በተከበረው ቁርኣናዊ አንቀጽ የሚከተለውን ተናግሯል፡-

﴿لَيْسَ كَمِثْلِهِ شَيْءٌ وَهُوَ السَّمِيعُ البَصِيرُ﴾

"የሚመስለው ምንም ነገር የለም። እርሱም ሰሚው ተመልካቹ ነው።" (አሸ'ሹራ፡ 11)

﴿قُلْ هُوَ اللَّهُ أَحَدٌ۞اللَّهُ الصَّمَدُ۞لَمْ يَلِدْ وَلَمْ يُولَدْ۞وَلَمْ يَكُن لَّهُ كُفُوًا أَحَدٌ﴾

"በል "እርሱ አላህ አንድ ነው። "አላህ (የሁሉ) መጠጊያ ነው። "አልወለደም ፤ አልተወለደምም። "ከእርሱም አንድም ቢጤ የለውም።" (አል'ኢኽላስ፡ 1-4)

﴿اللّهُ لاَ إِلَهَ إِلاَّ هُوَ الْحَيُّ الْقَيُّومُ لاَ تَأْخُذُهُ سِنَةٌ وَلاَ نَوْمٌ لَّهُ مَا فِي السَّمَاوَاتِ وَمَا فِي الأَرْضِ مَن ذَا الَّذِي يَشْفَعُ عِنْدَهُ إِلاَّ بِإِذْنِهِ يَعْلَمُ مَا بَيْنَ أَيْدِيهِمْ وَمَا خَلْفَهُمْ وَلاَ يُحِيطُونَ بِشَيْءٍ مِّنْ عِلْمِهِ إِلاَّ بِمَا شَاء وَسِعَ كُرْسِيُّهُ السَّمَاوَاتِ وَالأَرْضَ وَلاَ يَؤُودُهُ حِفْظُهُمَا وَهُوَ الْعَلِيُّ الْعَظِيمُ﴾

"አላህ ከእርሱ በቀር ኬላ አምላክ የለም። ሕያው ራሱን ቻይ ነው። ሚንገላጀትም እንቅልፍም አትይዘውም። በሰማያት ውስጥና በምድር ውስጥ ያለው ሁሉ የእርሱ ብቻ ነው። ያ እርሱ ዘንድ በፈቃዱ ቢሆን እንጅ የሚያማልድ ማነው? (ከፍጡሮች) በፊታቸው ያለውንና ከሁዋላቸው ያለውን ሁሉ ያውቃል። በሻውም ነገር እንጂ ከዕውቀቱ በምንም ነገር አያካብቡም (አያውቁም)። ኩርስዩ ሰማያትንና ምድርን ሰፋ። ጥበቃቸውም አያቅተውም። እርሱም የሁሉ በላይ ታላቅ ነው።" (አል'በቀራህ255)

ተውሒድን የሚያረጋግጡ ፣ ሽርክን የሚያወግዙ ፣ ለአላህ ሙሉ የሆኑ ባህሪያትን የሚያጸድቁ ፣ ጎደሎ እና ነውር ባህሪያትን ደግሞ የሚያስወግዱ ሌሎች የቁርኣን አንቀፆችና ምእራፎችም አሉ።

በዚህ ምክንያት ነብዩ ﷺ በፈጅር እና በጦዋፍ ሁለት ረከዓ የሱና ሶላት የሚከተለውን

ቁርአናዊ አንቀጽ ያነቡ ነበር፦

﴿قُولُواْ آمَنَّا بِاللّهِ وَمَا أُنزِلَ إِلَيْنَا وَمَا أُنزِلَ إِلَى إِبْرَاهِيمَ وَإِسْمَاعِيلَ وَإِسْحَاقَ وَيَعْقُوبَ وَالأسْبَاطِ وَمَا أُوتِيَ مُوسَى وَعِيسَى وَمَا أُوتِيَ النَّبِيُّونَ مِن رَّبِّهِمْ لاَ نُفَرِّقُ بَيْنَ أَحَدٍ مِّنْهُمْ وَنَحْنُ لَهُ مُسْلِمُونَ﴾

"በአላህና ወደኛ በተወረደው (ቁርአን) ወደ ኢብራሂምም ወደ ኢስማኢልና ወደ ያዕቁብና ወደ ነገዶችም በተወረደው በዚያም ሙሳና ዒሳ በተሰጡት በዚያም ነብያት ሁሉ ከጌታቸው በተሰጡት ከነርሱ በአንድም መካከል የማንለይ ስንሆን አመንን ፣ እኛም ከርሱ (ከአላህ) ታዛዦች ነን" በሉ።" (አል'በቀራህ፡ 136)

ይህ በተውሒድ አርሩቡብያ ላይ ትኩረት ያደረገ ነው። በሁለተኛው ረከዓ ደግሞ የሚከተለውን ያነቡ ነበር፦

﴿قُلْ يَا أَهْلَ الْكِتَابِ تَعَالَوْاْ إِلَى كَلَمَةٍ سَوَاء بَيْنَنَا وَبَيْنَكُمْ أَلاَّ نَعْبُدَ إِلاَّ اللّهَ وَلاَ نُشْرِكَ بِهِ شَيْئًا وَلاَ يَتَّخِذَ بَعْضُنَا بَعْضاً أَرْبَابًا مِّن دُونِ اللّهِ فَإِن تَوَلَّوْاْ فَقُولُواْ اشْهَدُواْ بِأَنَّا مُسْلِمُونَ﴾

"የመጽሐፉ ባለቤቶች ሆይ! በእኛና በእናንተ መካከል ትክክል ወደሆነች ቃል ኑ። (እርሷም) አላህን እንጅ ሌላን ላንገዛ ፣ በርሱም ምንንም ላናጋራ ፣ ከፊላችንም ከፊሉን ከአላህ ሌላ አሚልክት አድርጎ ላይይዝ ነው፤ በላቸው። እምቢ ቢሉም፡ - እኛ ሙስሊሞች መሆናችንን መስክሩ በሏቸው።" (አል'ዒምራን፡ 64)

ይህ የቁርአን አንቀጽ ደግሞ በሁለቱም የተውሂድ ክፍሎች - በተውሂድ አልኡሉሂያ ወይም በተውሂድ አልዒባዳ- ላይ ትኩረት ያደረገ ቁርአናዊ አንቀጽ ነው። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ በመጀመሪያው ረከዓ የሚከተለውን ቁርአናዊ አንቀጽ ያነቡ ነበር፦

﴿قُلْ يَا أَيُّهَا الْكَافِرُونَ۞لَا أَعْبُدُ مَا تَعْبُدُونَ۞وَلَا أَنتُمْ عَابِدُونَ مَا أَعْبُدُ۞وَلَا أَنَا عَابِدٌ مَّا عَبَدتُّمْ۞وَلَا أَنتُمْ عَابِدُونَ مَا أَعْبُدُ۞لَكُمْ دِينُكُمْ وَلِيَ دِينِ﴾

“በካቸው “እናንተ ከሐዲዎች ሆይ! “ያንን የምትግገዙትን (ጣዖት አሁን) አልገዛም። “እናንተም እኔ የምግገዛውን (አምካክም አሁን) ተገዢዎች አይደካችሁም። “እኔም ያንን የተገዛችሁትን (ወደፊት) ተገዢ አይደለሁም። “እናንተም እኔ የምግገዛውን (ወደፊት) ተገዢዎች አይደካችሁም። “ከእናንተ ሃይማኖታችሁ አልካችሁ። ከእኔም ሃይማኖቴ አለኝ።” *(አል’ካፊሩን፡ 1-6)*

ይህ ምዕራፍ በተውሂድ አልኡሉሁያ ወይም ተውሂድ አልዒባዳ (አምልኮታዊ) ላይ ትኩረት ያደረገ ምዕራፍ ነው። በሁለተኛው ረከዓ ደግሞ የሚከተለውን ይቀሩ ነበር፡-

﴿قُلْ هُوَ اللَّهُ أَحَدٌ۞اللَّهُ الصَّمَدُ۞لَمْ يَلِدْ وَلَمْ يُولَدْ۞وَلَمْ يَكُن لَّهُ كُفُوًا أَحَدٌ﴾

“በል “እርሱ አካህ አንድ ነው። “አካህ (የሁሉ) መጠጊያ ነው። “አልመለደም ፤ አልተመለደምም። “ከእርሱም አንድም ቢጤ የለውም።” *(አል’ኢኽላስ፡ 1-4)*

ይህ ምዕራፍ ደግሞ ተውሂደ ሩቡብያ እና ተውሂድ አስማእ ወስሲፋት ላይ ትኩረት ያደረገ ምዕራፍ ነው።

የአላህ መልእክተኛ ﷺ እነዚህን አንቀጾች በእነዚህ ሁለት ረከዓዎች ማንበባቸው አንደኛ ለህብረተሰቡ ተውሂድን ወይም ዓቂዳን በጥልቅ ለማስገንዘብ ፣ ሁለተኛ እያንዳንዱ ሙስሊም እራሱንም ይሁን ሌሎችን በዚህ ዓቂዳ ላይ እንዲያስታውስ በሶስተኛ ደረጃ ከእርሳቸው በኋላ የሚመጣው ሙስሊም ማህበረሰብ እነዚህን አንቀጾች በመቅራት ሱና አድርጎ እንዲይዘው ታሳቢ ያደረገ ነው።

ስለዚህ እነዚህ ምዕራፎች ሁለቱን የተውሂድ አይነት በውስጣቸው አቅፈዋል፡-

1. ተውሂድ አርሩቡብያ ፣ አስማእ ወስሲፋት
2. ተውሂድ አልዒባዳ ወልኡሉሁያ ናቸው

ይህ ዓቂዳ በመሰረቶች ላይ የተገነባ ነው። ይህንንም የአላህ መልእክተኛ ﷺ በጅብሪል ﷺ ሐዲስ ላይ ግልጽ አድርገውታል።

“ስለኢማን ንገረኝ?” በማለት ጅብሪል ረሡልን ﷺ ሲጠይቃቸው። (በዚህ ቦታ ኢማን ለማለት የተፈለገው ተውሒድን ነው።) የሚከተለውን ምላሽ ሰጡት፡-

"أن تؤمن بالله وملائكته وكتبه ورسله واليوم الآخر وتؤمن بالقدر خيره وشره"

“በአላህ ፣ በመላኢካዎች ፣ በመጽሐፍቶች ፣ በመልእክተኞች ፣ በመጨረሻው ቀን ልታምን ነው። መልካምም ይሁን ክፉ በአላህ ውሳኔ መሆኑን ልታምን ነው።”

(ሙስሊም፡ 8)

ኢማን ከስድስት ማዕዘናቶች የሚዋቀር መሆኑን አወሱ፡-

1. በአላህ ማመን
2. በመላኢካዎች ማመን
3. በመጽሐፎች ማመን
4. በመልእክተኞች ማመን
5. በመጨረሻው ቀን ማመን
6. መልካምም ይሁን ክፉ በአላህ ውሳኔ መሆኑን ማመን ናቸው።

እነዚህ የአህለሱና ወልጀማዓህ ዓቂዳ መሰረቶች ናቸው። ከዚህ መካከል ዋናው መሰረት ደግሞ በአላህ ማመን ነው። ይህ ዓቂዳ ፣ ቀጥተኛ ፣ ሰላማዊ ፣ ነብዩ ﷺ ጥሪ ያደረጉበት ፣ ለእርሱ ሲሉ የታገሉበት ፣ ለሶሃቦች ያስተማሩት ትክክለኛ ዓቂዳ ነው። ይህ ዓቂዳ ሙስሊሞች ከነብዩ ﷺ ወርሰው ከእነርሱም በኋላ ለመጣው ትውልድ ያወረሱት ዓቂዳ ነው። ይህ ዓቂዳ በእርሷ ላይ ህይወታችንን የምንመሰርትበት ፣ አጥብቀን የምንይዘው፣ ወደርሱ የምንጣራበት፣ እርሱን የተቃረነን አካል የምንታገልበት ዓቂዳ ነው።

አላህ በተከበረው ቁርኣናዊ አንቀጽ የሚከተለውን ተናግሯል፡-

﴿وَمَا أُمِرُوا إِلَّا لِيَعْبُدُوا اللَّهَ مُخْلِصِينَ لَهُ الدِّينَ حُنَفَاءَ وَيُقِيمُوا الصَّلَاةَ وَيُؤْتُوا الزَّكَاةَ وَذَلِكَ دِينُ الْقَيِّمَةِ﴾

"አላህን ሃይማኖትን ከእርሱ ብቻ አጥሪዎች ፣ ቀጥተኞች ሆነው ኪግዙት ፣ ሶላንም አስተካክለው ኪሰግዱ ዘካንም ኪሰጡ እንጅ ያልታዘዙ ሲሆኑ (ተከያዩ)። ይህ የቀጥተኛይቱ (ሃይማኖት) ድንጋጌ ነው።" *(አል'በይናህ፡ 5)*

ይህ ዲን ነው። ይህ ዓቂዳ ነው። ይህ በአላህ ማመን ነው።

እያንዳንዱ ሙስሊም ይህን ዓቂዳ መማር ፣ በእርሱም ማመን እና አላህን መገዛት አለበት። እኛ ዓቂዳችንን የምናረጋግጠው በኹራፋት (በልብ ወለድ አመለካከት) ፣ ከአባት ከአያት በተገኘ ጭፍን ተከታይነት ፣ በህልም ፣ በውሸት ቂሷ (ተረት) ፣ በክርክር ፣ በሎጂክ ወይም በፍልስፍና ሳይሆን በአላህ ኪታብ ነው። በዚህ ታላቅ መሰረትና ምንጭ ላይ ዓቂዳችንን እናረጋግጣለን። አቂዳችንን በሰለፎች ግንዛቤ በአላህ ኪታብና በረሡል ﷺ ሱና ላይ እንመሰርታለን።

ረሡል ﷺ የሚከተለውን ሐዲስ ተናግረዋል፡-

"تركتكم على البيضاء ليلها كنهارها لا يزيغ عنها بعدي إلا هالك"

"ከእኔ በኋላ ጠፊ ካልሆነ በቀር ከእርሷ የማይጠምባት ሌሊቷ ልክ አንደቀን በሆነች ጥርት ያለች ጎዳና ላይ ትቻችኋለሁ።" *(አህመድ፡ 17142, ኢብኑ ማጀህ፡ 43, ሐዲሱን አልባኒ ሶሂህ ብለውታል "አስ'ሲልሲለቱ አስ'ሶሂህ፡ 937)*

ይህን አቂዳ የሚቃረን አካል ጥፋት እንጅ ሌላ ነገር አይከተለውም። የአላህ መልእክተኛ ﷺ የሚከተለውን ሐዲስ ተናግረዋል፡-

"إن بني إسرائيل تفرقت على ثنتين وسبعين ملة ، وتفترق أمتي على ثلاث وسبعين ملة كلهم في النار إلا ملة واحدة"

“በኒኢስራኢሎች ከሰባ ሁለት ተከፍለዋል ፣ የእኔ ኡመት (ተከታዮች) ደግሞ ከሰባ ሶስት ይከፈላሉ። አንዷ ብቻ ስትቀር ሁሉም የእሳት ናቸው።”

“እርሷ ማን ነች?” በማለት ሶሃቦች ጥያቄ አቀረቡ። እርሳቸውም፦

"ما أنا عليه وأصحابي"

“እኔና ባልደረቦቼ በነበርንበት (ጎዳና ላይ የሆኑ)” (ቲርሚዚይ፡ 2641, አልባኒ ሐዲሱን ዶኢፍ ብለውታል “መሸካቱ አል’መሷቢህ፡ 171)

"فإنه من يعش منكم بعدي فسيرى اختلافا كثيرا، فعليكم بسنتي وسنة الخلفاء الراشدين المهديين، تمسكوا بها، وعضوا عليها بالنواجذ، وإياكم ومحدثات الأمور، فإن كل محدثة بدعة، وكل بدعة ضلالة "

“እንሆ ከእናንተ የቆየ ሰው ብዙ ልዩነቶችን ይመለከታል ፤ ሱናየን እንዲሁም የቅን (ጎዳና) መሪዎችና ምክትሎቼን ሱና አደራ ፣ በእርሷ አጥብቃችሁ ያዙ ፤ በመንጋጋ ጥርሳችሁ ነክሳችሁ ያዙ ፤ እናንተንም አደዲስ ፈጠራዎችንም አስጠነቅቃለሁ። አደዲስ ፈጠራዎች ቢድዓ ናቸው። ማንኛውም ቢድዓ ደግሞ ጥመት ነው።” (አህመድ፡ 17145, አቡዳውድ፡ 4607, ኢብኑ ማጀህ፡ 42, ዳሪሚይ፡ 96, ሐዲሱን አልባኒ ሶሂህ ብለውታል “አስሲልሲለቱ አስ’ሶሂህ፡ 2735)

“ማንኛውም ጥመት የእሳት ነው” የሚል በሌላ ዘገባ ተዘግቧል። (ነሳኢይ፡ 1578, ሐዲሱን አልባኒ ሶሂህ ብለውታል “አህከሙ አል’ጀናኢዝ፡ 294)

ይህ ነው አላህ የተናገረው ሰላማዊውና ቀጥተኛ ጎዳና።

አላህ በተከበረው ቁርኣናዊ አንቀጽ የሚከተለውን ተናግሯል፦

﴿وَأَنَّ هَـٰذَا صِرَاطِي مُسْتَقِيمًا فَاتَّبِعُوهُ وَلاَ تَتَّبِعُواْ السُّبُلَ فَتَفَرَّقَ بِكُمْ عَن سَبِيلِهِ ذَلِكُمْ وَصَّاكُم بِهِ لَعَلَّكُمْ تَتَّقُونَ﴾

“ይህም ቀጥተኛ ሲሆን መንገዴ ነው ፤ ተከተሉትም። (የጥመት) መንገዶችንም አትከተሉ። ከ (ቀጥተኛው) መንገዱ እናንተን ይከያዩዋችኋልና። እነሆ ትጠነቀቁ ዘንድ በርሱ አዘዛችሁ።” (አል’አንዓም፡ 153)

﴿وَاعْتَصِمُواْ بِحَبْلِ اللّهِ جَمِيعًا وَلاَ تَفَرَّقُواْ وَاذْكُرُواْ نِعْمَتَ اللّهِ عَلَيْكُمْ إِذْ كُنتُمْ أَعْدَاء فَأَلَّفَ بَيْنَ قُلُوبِكُمْ فَأَصْبَحْتُم بِنِعْمَتِهِ إِخْوَانًا وَكُنتُمْ عَلَى شَفَا حُفْرَةٍ مِّنَ النَّارِ فَأَنقَذَكُم مِّنْهَا كَذَلِكَ يُبَيِّنُ اللّهُ لَكُمْ آيَاتِهِ لَعَلَّكُمْ تَهْتَدُونَ﴾

"የአላህንም (የሚመን) ገመድ ሁላችሁም ያዙ። አትከፋፈሉም። ጠበኞችም በነበራችሁ ጊዜ በእናንተ ላይ (የዋለውን) የአላህን ጸጋ አስታውሱ። በልቦቻችሁም መካከል አስማማ። በጸጋውም ወንድማማቾች ሆናችሁ። በእሳት ጉድጓድ አፋፍም ላይ ነበራችሁ። ከእርሷም አዳናችሁ። እንደዚሁ ትመሩ ዘንድ አላህ ከእናንተ አንቀጾቹን ያብራራል።" *(አል'ዒምራን፡ 103)*

﴿إِنَّ هَذِهِ أُمَّتُكُمْ أُمَّةً وَاحِدَةً وَأَنَا رَبُّكُمْ فَاعْبُدُونِ﴾

"ይህች (ሕግጋት) አንዲት መንገድ ስትሆን በእርግጥ ሃይማኖታችሁ ናት። እኔም ጌታችሁ ነኝና ተገዙኝ።" *(አል'አንቢያእ፡ 92)*

በሰዎች መካከል የሚያስተሳስር ፣ የማህበረሰቡን ልቦና አንድ የሚያደርገው ዓቂዳ ይህ ነው።

አንዳንድ ጠማማ ሰዎች ዓቂዳዎችን መለያየት ሰዎችን ይከፋፍላል ፤ ይበታትናል ይላሉ። ፍላጎታቸው ምን እንደሆነ ታውቃላችሁ? ወደአላህ ጥሪ ማድረግ አያስፈልግም ማለታቸው እኮ ነው። ዳዕዋ ካደረግንም የዓቂዳን ጉዳይ መንካት የለብንም ማለታቸው እኮ ነው። ሱብሃን አላህ! ያለዓቂዳ ምን አይነት ዳዕዋ ነው የሚደረገው? በዓቂዳ መጀመር ፣ ዓቂዳን ማስተካከል የግድ ነው። ማህበረሰቡን ለማስተካከል ከተፈለገ ትክክለኛውን ዓቂዳ መሰረት ያደረገ ዳዕዋ ሊደረግ ይገባል። ሕብተሰቡን የሚከፋፍለው የተሳሳተ ዓቂዳ ፣ ጠማማ የሆነ መዝሐብ እና የተበላሸ አመለካከት እንጅ ትክክለኛ ዓቂዳ አይከፋፍልም።

ትክክለኛው ተውሒድ ፣ ሰላማዊ የሆነ ዓቂዳ ህዝብን ይሰበስባል ወይም አንድ ያደርጋል እንጅ አይከፋፍልም። በነብዩ ﷺ ዘመን ዓረቦችን እና አጀሞችን (ከዓረብ ውጭ የሆኑትን) ፣ ጥቁሩንም ነጩንም ፣ ምስራቁን ምዕራቡን አንድ ያደረገው ይህ ዓቂዳ ነው። እንዴት ዓቂዳ ሰዎችን ይከፋፍላል? !

አላህ በተከበረው ቁርኣናዊ አንቀጽ የሚከተለውን ተናግሯል፡-

﴿فَإِنَّ حَسْبَكَ اللهُ هُوَ الَّذِي أَيَّدَكَ بِنَصْرِهِ وَبِالْمُؤْمِنِينَ۞وَأَلَّفَ بَيْنَ قُلُوبِهِمْ لَوْ أَنفَقْتَ مَا فِي الأَرْضِ جَمِيعاً مَّا أَلَّفْتَ بَيْنَ قُلُوبِهِمْ وَلَكِنَّ اللهَ أَلَّفَ بَيْنَهُمْ إِنَّهُ عَزِيزٌ حَكِيمٌ﴾

"እርሱ ያ በእርዳታውና በምእምናን ያበረታህ ነው። በልቦቻቸውም መካከል ያስማማ ነው። በምድር ያለውን ሁሉ (ሐብት) በከገለክ ኖሮ በልቦቻቸው መካከል ባላስማማህ ነበር። ግን አላህ በመካከላቸው አስማማ። እርሱ አሸናፊ ጥበበኛ ነውና።" *(አል'አንፋል፡62-63)*

በተውሂድ ዓረቦችን እና አጀሞችን አንድ ያደረገውና ሶሃቦች ይዘውት በመጡት ሰላማዊ ዓቂዳ ካልሆነ በቀር ልቦች አይሰባሰቡም ፣ ህብረተሰቡም አንድ ሊሆን አይችልም።

አላህ በተከበረው ቁርኣናዊ አንቀጽ የሚከተለውን ተናግሯል፡-

﴿وَاعْتَصِمُواْ بِحَبْلِ اللهِ جَمِيعًا وَلاَ تَفَرَّقُواْ وَاذْكُرُواْ نِعْمَتَ اللهِ عَلَيْكُمْ إِذْ كُنتُمْ أَعْدَاء فَأَلَّفَ بَيْنَ قُلُوبِكُمْ فَأَصْبَحْتُم بِنِعْمَتِهِ إِخْوَانًا وَكُنتُمْ عَلَى شَفَا حُفْرَةٍ مِّنَ النَّارِ فَأَنقَذَكُم مِّنْهَا كَذَلِكَ يُبَيِّنُ اللهُ لَكُمْ آيَاتِهِ لَعَلَّكُمْ تَهْتَدُونَ﴾

"የአላህንም (የሚመን) ገመድ ሁላችሁም ያዙ። አትከፋፈሉም። ጠበኛችሁም በነበራችሁ ጊዜ በእናንተ ላይ (የዋለውን) የአላህን ጸጋ አስታውሱ። በልቦቻችሁም መካከል አስማማ። በጸጋውም ወንድማማቾች ሆናችሁ። በእሳት ጉድጓድ አፋፍም ላይ ነበራችሁ። ከእርሷም አዳናችሁ። እንደዚሁ ትመሩ ዘንድ አላህ ከእናንተ አንቀጾቹን ያብራራል።" *(አል'ዒምራን፡103)*

ሶሃቦች በተውሂድ ምክንያት እርስ በርስ የሚገዳደሉ ጠላቶች በመሆን ምትክ የሚዋደዱ ወንድማማቾች ሆኑ።

ዓቂዳችን በተለያዩ የጠማማ አመለካከቶች ፣ መዝሀቦች ፣ ውሸት በሆኑ እምነቶች እንዲሸፈን አንፈቅድም። የወደደ ይውደድ የጠላ ይጥላ ሐቅና ባጢሉ የግድ መለየት አለበት። እኛ በስህተት ጎዳና ሰውን መሰብሰብ የለብንም። መሰብሰብ ያለብን በሐቅ ላይ መሆን አለበት።

ኢማሙ ማሊክ ﷺ የሚከተለውን ተናግረዋል፡-

"لا يصلح آخر هذه الأمة إلا ما أصلح أولها"

"የመጨረሻውን ትውልድ የሚያስተካክለው የለም የመጀመሪያውን ትውልድ ያስተካከለው ቢሆን እንጅ" (መጅሙዕ አል'ፈታዋ፡ 20/375)

በዓቂዳ ላይ ያልተመሰረተ ፣ ለዓቂዳ መፍትሄ ያልሰጠ ዳዕዋ ውጤት አልባ ነው የሚሆነው። ማስተካከል ሳይሆን ማበላሸት ነው የሚሆነው።

ሙስሊሞች ትክክለኛ በሆነ የዓቂዳ ኪታቦች ላይ ትኩረት ሊሰጡ ይገባል። ሙስሊሞች የረሡል ﷺ ዲን ህያው ልትሆን ዘንድ ትክክለኛ የዓቂዳ ኪታቦችን መማር ፣ ማስተማር እንዲሁም ለሰዎች በሰፊው ማሰራጨት ይኖርባቸዋል።

ረሡል ﷺ የሚከተለውን ተናግረዋል፡-

"إني تارك فيكم ما إن تمسكتم به لن تضلوا بعدي: كتاب الله وسنتي"

"ከእኔ በኋላ በእናንተ ውስጥ አጥብቃችሁ ከያዛችሁት የማትጠመሙበትን ትቸ (ሔጀከሁ) ፡ የአላህ ኪታብና የእኔ ሱና ነው" (ቲርሚዚይ፡ 3788, ሐዲሱን አልባኒ ሶሂህ ብለውታል "ሶሂህ አል'ጃሚዕ፡ 2458)

ይህን ጉዳይ አረሳስተን ከአቂዳ ውጭ መሰባሰብን እና መተሳሰርን የምንፈልግ ከሆነ ኪሳራና አጉል ልፋት ነው የሚገጥመን። ምክንያቱም ከቁርኣን እና ከሀዲስ በተያዘ ትክክለኛ አቂዳ እንጅ ልቦች ሊሰባሰቡ አይችሉም።

አንተ አላህ ይህን.. ይህን ተናገረ ፤ ረሡል ﷺ ይህን ይህን.. ተናገሩ ብለህ ብትናገር ሰዎች ያለምንም መጠራጠር ሙሉ በሙሉ ይቀበሉሃል። ነገር ግን እከሌ ይህን አለ ፣ እከሌ ደግሞ ይህን አለ.. የምትል ከሆነ ሰዎች አይቀበሉህም። ሰዎች በአንተ ዙሪያ ሊሰባሰቡ አይችሉም። ሰዎችን አንድ የሚያደርጋቸው አላህ ይህን አለ ፣ ረሡል ﷺ ይህን አሉ የምትል ከሆነ ነው። ልክ እንደዚሁ ሙስሊሞችን የሚሰበስባቸው ጥርት ያለው የተውሂድ ቃል ነው። ሰዎችን የሚሰበስባቸው ረሡል ﷺ ለእኛ አደራ ብለውና ትተውልን የሄዱት ዓቂዳ ነው። እርሱም የተውሂድ ቃል ነው። እርሱም የኢስላማዊ ዓቂዳ ነው። እርሱም በአላህ ጌትነት ፣ በኢስላም ትክክለኛ ሀይማኖትነት ፣ በሙሀመድ መልክተኛነት እና ነብይነት ማመን ነው።

ረሡል ﷺ የሚከተለውን ተናግረዋል፡-

"إن الله يرضى لكم ثلاثا ويسخط لكم ثلاثا، يرضى لكم أن تعبدوه ولا تشركوا به شيئا، وأن تعتصموا بحبل الله جميعا ولا تفرقوا، وأن تناصحوا من ولاه الله أمركم..

"አላህ ከአናንተ ሶስት ነገሮችን ይወዳል ፣ ሶስት ነገሮችን ደግሞ ይጠላል። ከአናንተ በአርሱ አንድንም አንዳታጋሩ፣ አላህን ብቻ አንድትግገዙ ፤ ሁላችሁም በአላህ ገመድ አንድትጠበቁ ፣ አንዳትለያዩ ፤ አላህ የአናንተን ጉዳይ ለማስተዳደር ከሾመው አካል ጋር አንድትመካከሩ ..." (ሙስሊም፡ 1715)

"አላህን ልትገዙ በአርሱም አንድም ነገር ላታሻርኩ (ላተጋሩ)" አላህን ብቻ ማምለክ፣

መስለሞችን ይሰበስባል ፣ አንድ ያደርጋል። አላህን ብቻ መግዛት በልቦች መካከል ወንድማማች ያደርጋል። መስለሞች ጌታቸው አንድ ፣ የሚያመልኩት አንድ ብቻ ነው።

ነብዩሏህ ዩሱፍ ﷺ የሚከተለውን ተናግሯል፡-

﴿يَا صَاحِبَيِ السِّجْنِ أَأَرْبَابٌ مُّتَفَرِّقُونَ خَيْرٌ أَمِ اللهُ الْوَاحِدُ الْقَهَّارُ۞مَا تَعْبُدُونَ مِن دُونِهِ إِلاَّ أَسْمَاء سَمَّيْتُمُوهَا أَنتُمْ وَآبَآؤُكُم مَّا أَنزَلَ اللهُ بِهَا مِن سُلْطَانٍ إِنِ الْحُكْمُ إِلاَّ لِلّهِ أَمَرَ أَلاَّ تَعْبُدُواْ إِلاَّ إِيَّاهُ ذَلِكَ الدِّينُ الْقَيِّمُ وَلَكِنَّ أَكْثَرَ النَّاسِ لاَ يَعْلَمُونَ﴾

"የተለያዩ አምላኮች ይሻላሉን ወይስ አሸናፊው አንዱ አላህ "ከእርሱ ሌላ እናንተና አባቶቻችሁ (አማልክት ብላችሁ) የጠራችኋቸውን ስሞች እንጅ አትግገዙም። አላህ በእርሷ ምንም አስረጅ አላወረደም። ፍርዱ የአላህ እንጅ የሌላ አይደለም። እርሱን እንጅ ሌላን እንዳትገዙ አዟል። ይህ ትክክለኛው ሃይማኖት ነው። ግን አብዛኞቹ ሰዎች አያውቁም።" *(ዩሱፍ፡ 39-40)*

ይህ ዓቂዳችን ነው ፤ ይህ ዲናችን ነው ፤ ይህ ዳዕዋችን ነው ፤ ይህ የአላህ ኪታብ እና የነብዩ ﷺ ሱና ነው። ይህ መንሐጃችን (የምንከተለው ጎዳና) ነው።

ልቦቻችንን በኢማን ፣ በትክክለኛው ዓቂዳ ላይ እንዲሰበስብልን ፤ እናንተንም እኛንም ከፈተና ፣ ከተንኮል ፣ ከጥመት ፣ ግልጽም ይሁን ስውር ከሆነው ሐጢያት እንዲጠብቀን አላህን እንማጸናለን።

وصلى الله على نبينا محمد وعلى آله وأصحابه أجمعين

ጥያቄ

ጥያቄ 1፡- በተውሂድ አገር የሚኖሩ ሰዎች ተውሂድን መማር አያስፈልጋቸውም በማለት ቅስቀሳ የሚያደርጉና ሰዎችን ከተውሒድ ትምህርት እንዲርቁ የሚያደርጉ ሰዎች አሉ። ለዚህ የሚሰጡን ምላሽ ካለ?

መልስ 1፡ - እንዲህ አይነት ንግግር የሚናገረውን ሰው "እስኪ ተውሂድ ምን እንደሆነ ንገረን ፤ ትረጉሙንም አብራራልን" ብለን ብንጠይቀው መተርጎምም ማብራራትም አይችልም። "የኢማን ማዕዘናቱ ስንት ነው?" ፣ "የኢስላም ማዕዘናት ስንት ነው?" "ኢህሳን ማለት ምን ማለት ነው?" ብለን ብንጠይቀው እንዲሁ ሊያብራራልን አይችልም። እርሱ ግን እኔ በተውሂድ ላይ ነኝ ብሎ ይሞግታል። እርሱ ተውሂድን ሳያውቅ እንዴት በተውሂድ ላይ ሊሆን ይችላል? "ሽርክ ምንድን ነው?" "አይነቱ ምንድን ነው" "ከኢስላም የሚያስወጣው የቱ ነው?" "ከኢስላም የሚያስወጣው የቱ ነው?" "ኒፋቅ ምንድን ነው?" አይነቶቹ ምን ምን ናቸው?" ብለን ብንጠይቀው መልስ ሊሰጠን አይችልም።

እርሱ ግን "እኛ የተውሂድ ሰዎች ነን" ይላል። አዎ በንግግር የተውሂድ ሰዎች ሊሆን ይችላል። ይህን ንግግር የሚናገረው ሰው ግን ተውሂድን አያውቀውም። ረሡል ﷺ መካ ውስጥ ስለተውሂድ ብቻ ጥሪ እያደረጉ አስራ ሶስት አመት መቆየታቸውን አያውቅም። ኑህ ዘጠኝ መቶ አምሳ አመት ወደተውሂድ እየተጣራ መቆየቱን አያውቅም።

አላህ በተከበረው ቁርአናዊ አንቀጽ የሚከተለውን ተናግሯል፡-

﴿يَا قَوْمِ اعْبُدُواْ اللّهَ مَا لَكُم مِّنْ إِلَهٍ غَيْرُهُ﴾

“ወገኖቹ ሆይ! አላህን ተገዙ። ከእናንተ ከርሱ ሌላ ምንም አምላክ የላችሁም።”

(አል’አዕራፍ፡ 59)

﴿قَالَ يَا قَوْمِ إِنِّي لَكُمْ نَذِيرٌ مُّبِينٌ۝أَنِ اعْبُدُوا اللَّهَ وَاتَّقُوهُ وَأَطِيعُونِ۝يَغْفِرْ لَكُم مِّن ذُنُوبِكُمْ وَيُؤَخِّرْكُمْ إِلَى أَجَلٍ مُّسَمًّى إِنَّ أَجَلَ اللَّهِ إِذَا جَاء لَا يُؤَخَّرُ لَوْ كُنتُمْ تَعْلَمُونَ۝قَالَ رَبِّ إِنِّي دَعَوْتُ قَوْمِي لَيْلًا وَنَهَارًا۝فَلَمْ يَزِدْهُمْ دُعَائِي إِلَّا فِرَارًا۝وَإِنِّي كُلَّمَا دَعَوْتُهُمْ لِتَغْفِرَ لَهُمْ جَعَلُوا أَصَابِعَهُمْ فِي آذَانِهِمْ وَاسْتَغْشَوْا ثِيَابَهُمْ وَأَصَرُّوا وَاسْتَكْبَرُوا اسْتِكْبَارًا۝ثُمَّ إِنِّي دَعَوْتُهُمْ جِهَارًا﴾

(የውሳኔው) ጊዜ በመጣ ወቅት አይቆይም። የምታውቁት ብትሆኑ ኖሮ (በታዘዛችሁ ነበር)።” (ስለተቃወመውትም) “አከ ጌታዬ ሆይ! እኔ ሌሊትም ቀንም ሕዝቦቼን ጠራሁ። “ጥሪየም መሸሽን እንጅ ሌላ አልጨመረላቸውም። “እኔም ከእነርሱ ትምር ዘንድ (ወደእምነት) በጠራኋቸው ቁጥር ጣቶቻቸውን በጀሮዎቻቸው ውስጥ አደረጉ። ልብሶቻቸውንም ተከናነቡ። (በመጥፎ ስራቸው ላይ) ዘመተሩም። (ያለፈን) መኩራትንም ኮሩ። “ከዚያም እኔ በጩኸት ጠራኋቸው። “ከዚየም እኔ ከእነርሱ ገለጽኩ። ከእነርሱም መመስጠርን መሰጠርኩ።” *(ኑሕ 2-9)*

ተውሂድ ትኩረት የሚፈልግ እንጅ ቀላል ጉዳይ አይደለም። ተውሂድን መማር ፣ ማወቅ ያስፈልጋል። የተውሂድን አፍራሽ ፣ የተውሂድን አበላሽ ሳታውቅ እኔ የተውሂድ ሰው ነኝ ማለቱ ብቻ በቂ ሊሆን አይችልም። አንተ ሳታውቅ እንዴት እኔ የተውሂድ ሰው ነኝ ትላለህ? አንተ በተውሂድ ከነብዩ ኢብራሂም ﷺ ትበልጣለህ? ነብዩ ኢብራሂም ﷺ በዱዓቸው ውስጥ የሚከተለውን ነው የተማጸኑት፡-

﴿وَإِذْ قَالَ إِبْرَاهِيمُ رَبِّ اجْعَلْ هَذَا الْبَلَدَ آمِنًا وَاجْنُبْنِي وَبَنِيَّ أَن نَّعْبُدَ الأَصْنَامَ۝رَبِّ إِنَّهُنَّ أَضْلَلْنَ كَثِيراً مِّنَ النَّاسِ فَمَن تَبِعَنِي فَإِنَّهُ مِنِّي﴾

"ኢብራሂምም ባከ ጊዜ (አስታውስ) "ጌታዬ ሆይ! ይህንን አገር (መካን) ጸጥተኛ አድርገው። እኔንም ልጆቼንም ጣዖታትን ከመገዛት አርቀን። ጌታዬ ሆይ! እነዚህ (ጣዖታት) ከሰዎች ብዙዎችን አሳስተዋልና። የተከተለኝም ሰው እርሱ ከኔ ነው።" (ኢብራሒም፡ 35-36)

ተመልከቱ ኢብራሒም ለነፍሱ ሽርክን ሲፈራ ይህ ተናጋሪ ግን ሽርክ እኔን ምንም አይነካኝም ብሎ እየተማመነ ነው። እኔ የተውሂድ ሰው ነኝ እያለን ነው። አላህን አይፈራም? ይህን የሚናገረው ሰው ጃሂል ወይም ከትክክለኛ ዓቂዳ ሰዎች እንዲሸሹ ለማድረግ የሚጥር ጠማማ ሰው ነው።

ጥያቄ 2፡- ዓቂዳቸው የተበላሸ ምዕራባውያን ማህይማን ሙስሊሞች ባለማወቃቸው ምክንያት (ኡዝር) ሊሰጣቸው ይችላል? ከምእራብ በኩል ዓሊም የለም ተብሎ ነው የሚታወቀው።

መልስ 2 - የሚያስተምረው እና የሚያብራራለት አካል እያለ አንድ ሰው ባለማወቁ ምክንያት አይሰጠውም። በምዕራብም ይሁን በምስራቅ ምስጋና ለአላህ ይገባው ዓሊሞች ተሰራጭተዋል። ወደአላህ የሚደረገው ዳዕዋ ተሰራጭቷል። ትክክለኛው ዓቂዳ ተብራርቷል። ከሽርክ የሚከለክል ከዓቂዳ ብልሹነት የሚያብራሩ የመገናኛ ዘዴዎች ተሰራጭተዋል። እንደዚሁ መጽሀፎችም ተሰራጭተዋል። እውቀት ያልደረሳቸው ፣ ያልሰሙ ፣ ማንበብ የማይችሉ ግለሰቦች ካልሆኑ በቀር በመካከላቸው ዲኑን የሚያብራሩ ዓሊሞች እያሉ አለማዎቃቸው ምክንያት አያሰጣቸውም። አላህ በምድር ላይ ሁጃን አቁሟል። ምክንያት የሚሰጣቸው ሰዎችም በጣም አናሳ ናቸው።

ጥያቄ 3፡- በፊት የነበሩ የኸዋሪጅ ፣ የሙዕተዚላ እና ሌሎች አንጃዎች ሙሉ በሙሉ

ጠፍተዋል። ስለነርሱ ማውራቱ ምን ጥቅም አለው። ስለነርሱ ማውራቱ ጊዜን ማቃጠል ነው የሚሉ ሰዎች አሉ። እነዚህ ሰዎች ሙስሊሞች እንደሚከፋፈል የአላህ መልእክተኛ ﷺ የተናገሩትን ሐዲስ ደካማ ነው ይላሉ። ለዚህ የሚሰጡን ምላሽ ካለ?

መልስ 3፡- አንጃዎች አላለቁም። አሁን ይገኛሉ። ሙዕተዚላ ይገኛል። ጀህምያ በአሁኑ ሰዓት በሀይለኛው ስለመንሐጃቸው ቅስቀሳ እያደረጉ ይገኛሉ። የመቃብር አምላኪዎች አሁን ይገኛሉ። ሁሉም የጥመት አንጃዎች በአሁኑ ሰዓት ይገኛሉ። መጽሐፋቸው በአሁኑ ሰዓት እየተታመ ፣ እየተሰራጨ ይገኛል። እንዴት አሁን አይገኙም ፣ አልቀዋል ይላሉ? ይህ ሰው አንድም የተነባበረ ማህይምነት ያለበት ወይም ሰውን ከሐቅ ለማሸሽ የሚንቀሳቀስ ጠማማ ሰው ነው። ይህ ቅስቀሳ አሁንም አለ። አትከፋፍሉን ፣ ሙስሊሞች ከአላህ ውጭ ቢያመልኩም ፣ ከአላህ ውጭ ቢያርዱም ፣ ሶላትን ቢተውም ፣ አላህን ከመታዘዝ ቢያምጹም ሙስሊም የሚለው ስም ብቻ ይበቃቸዋል የሚሉ አሉ።

ይህ አካሄድ የተባለሽ አካሄድ ነው። አፍራሽ መዝሐብ ነው። ወደርሱ ፊታችንን ልናዞር አይገባም።ሙስሊም መባላችን ብቻ በቂ አይደለም።የግድ ኢስላምን ማረጋገጥ አለብን።

ረሡል ﷺ የሚከተለውን ሐዲስ ተናግረዋል፡-

"الإسلام أن تشهد أن لا إله إلا الله، وأن محمدا رسول الله، وتقيم الصلاة، وتؤتي الزكاة، وتصوم رمضان، وتحج البيت إن استطعت إليه سبيلا"

“ኢስላም ማለት ከአላህ በቀር በአውነት የሚመለክ አምላክ የለም ብለህ ልትመሰክር ፣ ሙሀመድ የአላህ መልአክተኛ ናቸው ብለህ ልትመሰክር ፣ ሶላትን ደንቡን ጠብቀህ ልትሰግድ ፣ ዘካን ልትሰጥ ፣ የረመዷንን ጾም ልትጾም ፣ መንገድን የቻለ ሰው የአርሱን ቤት ሒጎበኝ ነው።” *(ቡኻሪ፡ 4777, ሙስሊም፡ 8)*

ጥያቄ 4፡- ከሶላት ፈርዶች አንዱን ፈርድ የተወ ሰው ብይኑ ምንድን ነው? ለምሳሌ፡ ዛሬ የፈጅርን ሶላት ሆን ብሎ ይተወዋል። ከፈጅር ቀጥሎ ያለውን ሶላት ይሰግዳል። ይህ ሰው ካፊር ይሆናል?

መልስ 4፡- ሶላትን ሆን ብሎ የተወ ሰው ካፊር ነው። ወደአላህ ተጸጽቶ መመለስ ግዴታ አለበት። በአዲስ መልክ ወደኢስላም መግባት አለበት። ምክንያት (ኡዝር) ሊሰጠው የሚችለው እንቅልፍ አሸንፎት ወይም ተኝቶ ወይም ረስቶ ሶላት ያመለጠው ሰው ብቻ ነው።

የአላህ መልእክተኛ ﷺ የሚከተለውን ተናግረዋል፡-

"من نسي صلاة فليصلها إذا ذكرها لا كفرة لها إلا ذلك" وفي لفظ له: (من نسي صلاة أو نام عنها)

"ሶላትን የረሳ ሰው ሲያስታውስ ይስገዳት አርሱ አንጅ ኬላ ካፋራ (ማካካሻ) የለውም።" በኬላ ዘገባ "ሶላትን የረሳ ወይም አንቅልፍ ተኝቶ ያሳለፋት) *(ሙስሊም፡684)*

ሆን ብሎ የተዋት ሰው ይሰገዳት አላለም። አንድ ሶላት እንኳ ቢሆን ሆን ብሎ ከተዋት ይክፍራል።

ይህን አስመልክቶ የሚከተለው ሐዲስ መጧል፡-

"من ترك صلاة العصر فقد حبط عمله"

"የዓስርን ሶላት የተወ ሰው ስራው በአርግጥ ተሰረዘ" *(ቡኻሪ፡594)*

ከወቅቱ ከወጣ አምልጦታል ማለት ነው። ማለትም ይህ ሰው በወቅቷ ሆን ብሎ አልሰገደም። ሆን ብሎ ካልሆነ ግን ይህ ሰው ምክንያት ይሰጠዋል። ነገር ግን ቀደ ማውጣት አለበት።

ጥያቄ 5፡- የተውሂድን እና የዓቂዳን ጉዳይ የሚያቃልሉ አንዳንድ መጽሐፎችን በማየታችን በጣም አዝነናል። ለዚህ የሚሰጡን አስተያየት ምንድን ነው?

መልስ 5፡- የዓቂዳን እና የተውሂድን ጉዳይ ለማቃለል ቅስቀሳ በማድረግ የተሰለፉ ሰዎች አሉ። አላማቸው ሁሉንም ሰው በአንድ አይነት በመመልከት የመቀላቀል ሐሳብ ነው። እነዚህ ሰዎች አንድ ሰው የዲን ስራዎችን ባይሰራም ፣ ከአላህ ውጭ ቢጣሩም ፤ ከአላህ ውጭ ቢያርዱም ፤ በሙታን እና በቀብር የሙጥኝ ቢሉም ሙስሊም በሚል መጠራቱ ወይም በእርሱ ጥላ ስር መሰባሰብ ብቻ በቂህ ነው የሚሉ ናቸው።

ጥያቄ 6፡- በእንቅልፍ ላይ እያለሁ ስፐርም ወይም መዝይ (ወፈር ያለ ፈሳሽ) በብልቴ ወጣብኝ ፣ ሳላውቅ የጁሙዓን ሶላት ሰገድኩ። ከዓስር ሶላት በኋላ የእስፐርሙን ምልክት አየሁት ምን ልስራ?

መልስ 6፡- በእንቅልፍ ልቡ ስፐርም ከወጣው ይህ ኢህቲላም በመባል ይጠራል። ገላውን ታጥቦ ውዱእ ካደረገ በኋላ ዙሁርን እና ዓስርን ቀጺ ብሎ ይስገድ።

ጥያቄ 7፡ - በመግሪብ ሶላት መጀመሪያ ረከዓ ላይ ሱረቱል ካፊሩን ፤ በሁለተኛው ረከዓ ላይ ደግሞ ሱረቱል ኢኽላስን ነብዩ ﷺ ቀርተዋል የሚል ወሬ ሰምቸ ነበር። ይህን በተመለከተ የተረጋገጠ ሐዲስ ይኖራል?

መልስ 7፡- እነዚህ ምእራፎች ሁልጊዜ ሳይሆን አልፎ አልፎ ከመግብሪብ በኃላ ካለው ሱና ላይ ይቀራሉ።

ጥያቄ 8፡- ዓቂዳን እና ተውሂድን ለመማር ደረጃው እንዴት ነው?

መልስ፡ 8፡- በስርአተ ትምህርት የሚመራ ትምህርት ቤት ከሆነ የተውሂድ ፣ የፊቅህ ፣

የሐዲስ ፣ የተፍሲር ፣ የዓረብኛ ቋንቋ ደረጃውን ጠብቆ ይሰጣል። በዑለሞች አማካኝነት በመስጅድ የሚቀራ ከሆነ ግን ዓሊሙ ለተማሪዎች በሚሰጠው አቅጣጫ መሰረት አጫጭር ኪታቦች በቅድሚያ ይቀራሉ። ከዚያም ደረጃውን ጠብቆ ሌሎች ኪታቦች ይቀራሉ።

ጥያቄ 9፡- የከሀዲዎች ስም የተጻፈበት የስፖርት ልብስ መልበስ ሸሪዓዊ ብይኑ ምንድን ነው?

መልስ 9፡- የከሀዲዎች ስም የተጻፈበት ልብስ ወይም ምስል መልበስ ከሀዲዎችን ከማላቅ እና ከማክበር ይቆጠራል። በልብስህ ላይ በጀርባም ይሁን ፊት ለፊት ስእል የተባለ ነገር አትልበስ። የሐዲዎችን ስም ተሸክመህ አትዙር። በማወደስና ወሰን በማለፍ የሙስሊም ስም ልብስ ላይ መጻፍ ከተከለከለ የከሀዲዎች እንዴት ሊሆን ነው?

ጥያቄ 10፡- አንዳንድ ሰዎች በዚህች አገር የሚገኙ ዓሊሞችን ሲተቿቸው ፣ ባልሆነ ገጽታ ሲስሏቸው ይስተዋላል ይህ እንዴት ይታያል?

መልስ 10፡- የዚህች አገር ዓሊሞች - ምስጋና ለአላህ ይገባው - የዓቂዳ ፣ የዳዕዋ ፣ የሐቅ ዓሊሞች ናቸው። እነርሱን የሚተች ከሆነም ምክንያቱን ይግለጽ። ዝም ብሎ የተውሂድ የዓቂዳ ዓሊሞች ስለሆኑ ብቻ ስሜቱን ተከትሎ የሚጠላቸው ከሆነ ለልቦናው መበላሸት መረጃ ነው። የመልካም ባለቤትን የሚጠላ የለም የተንኮል ባለቤት ቢሆን እንጅ።

ጥያቄ 11፡- አንዳንድ ሰዎች ዲን በልብ ነው በሚል መርሆ ውጫቸውን የማያሳምሩ አሉ። ጸጉራቸውን ከፊሉን አሳድገው ከፊሉን ይላጫሉ። ዋናው ነገር ቀልብ ነው ይላሉ። ለዚህ የሚሰጡን አስተያየት ካለ?

መልስ 11፡- ይህ እርስ በእርስ የሚቃረን ነው። ዲን በልቡ ቢኖር ኖሮ ውጪ ያምር ነበር። የውጪ ማማር ለልቡ ማማር ምልክት ነው። የውጪ መበላሸት የቀልቡ መበላሸትን ያመላክታል። እኛ በቀልብ ውስጥ ያለውን አላህ እንጅ ማንም የሚያውቅ የለም። ነገር ግን እኛ ውጪን አይተን ነው ፍርድ የምንሰጠው። ሱናን ቀጥ አድርጎ የሚከተል ከሆነ በመጥፎ አንጠረጥረውም። ጥርጣሬያችንን እናሳምራለን። በዲን የሚያሾፍ ከሆነ ግን ውስጤ ኢማን አለ ቢል እንኳ በመጥፎ እንጠረጥረዋለን። ውስጡን ወደአላህ ነው የምናስጠጋው። መልካም ይፋ ላረገልን እንቀበለዋለን። መጥፎን ይፋ ላደረገ ደግሞ እንተወዋለን።

ጥያቄ 12፡- አስራ አንድ አመት የሞላው ልጅ ወላጆቹ ስለሶላት ሳያስተምሩት ሞተ። ይህ ልጅ ለአቅመ አዳም ሳይደርስ ስለሶላት ከአላህ ዘንድ ሂሳብ ይደረጋል?

መልስ 12፡- መጀመሪያ ፣ ወላጆች ለልጁ አቅጣጫና ትምህርት ባለመስጠታቸው ተጠያቂ ይሆናሉ። ሁለተኛ፣ ለአቅመ አዳም ደርሶ ፣ ሙስሊሞች እየሰገዱ እየተመለከተ ፣ አዛንን እየሰማ ሆን ብሎ ሶላትን ከተወ ይህ ሰው ካፊር ነው። ከሙስለሞች አገር የራቀ ፣ ሆን ብሎ ሶላትን ያልተወ ከሆነ ደግሞ የእርሱን ጉዳይ ወደአላህ ነው የምናስጠጋው።

ጥያቄ 13፡- በአገራችን ሱናን አጥብቀን በመያዛችን ፣ ጺም በማሳደጋችን ምክንያት እንቸገራለን ፣ ከፍተኛ ጫናም ይደረግብናል በዚህ ምክንያት ጺማችንን ለመላጨት እንገደዳለን። ምን አቅጣጫ ይሰጡናል?

መልስ 13፡- ጢምን መላጨት አይፈቀድም። ምክንያቱም ወንጀል ነው። ነገር ግን የሚደርስባችሁን መከራ በመታገስ ላይ አደራ እላችኋለሁ። መጥፎ ቢደርስባችሁም

ዲናችሁን አደራ አጥብቃችሁ ያዙ። ከስቃይ ሰላም ለመሆን ብላችሁ ከዲናችሁ አትውረዱ። ታገሱ እናንተ ከፍተኛ ምንዳን ታገኛላችሁ።

ጥያቄ 14፡- አንዳንድ ሰዎች ብዛትን እንደማስረጃ በመጠቀም የሚታለሉ ሰዎች አሉ። ብዛትን ለሐቅ ማስረጃ አድርገውም ያቀርባሉ። ባጢል ወይም ውሸት ይዘው እንደዚህ ሊሰባሰቡ አይችሉም ይላሉ። ለዚህ የሚሰጡን አቅጣጫ ካለ?

መልስ 14፡- ለዚህ ጥያቄ መልሱ የሚከተለው ቁርኣን ነው፡-

አላህ በተከበረው ቁርአናዊ አንቀጽ የሚከተለውን ተናግሯል፡-

﴿وَإِن تُطِعْ أَكْثَرَ مَن فِي الأَرْضِ يُضِلُّوكَ عَن سَبِيلِ اللهِ﴾

"በምድርም ካሉት ሰዎች አብዛኞቹን ብትከተል ከአላህ መንገድ ያሳስቱሃል።"

(አል'አንዓም፡ 116)

﴿وَمَا أَكْثَرُ النَّاسِ وَلَوْ حَرَصْتَ بِمُؤْمِنِينَ﴾

"አብዛኞቹም ሰዎች (ከሚመናቸው) ብትጓጓም የሚያምኑ አይደሉም" *(ዩሱፍ፡ 103)*

ብዛት ለሐቅ ማስረጃ ሊሆን አይችልም። ብዛት አንዳንድ ጊዜ ለጥመትም ሊሆን ይችላል። በሐቅ ላይ ሆነው ቁጥራቸው ከበዛ ይህ መልካም ነው። ያለ ሐቅ ብዛት ምንም ዋጋ የለውም። ትንሾች በሐቅ ላይ ከሆኑ ብዙ ሆነው ባጢልን ከሚከተሉት የተሻሉ ናቸው። ትኩረት የሚሰጠው በብዛት ወይም በማነስ ሳይሆን በሐቅ ላይ መሆኑ ነው።

ጥያቄ 15፡- በከሀዲዎች አገር በቋሚነትም ይሁን በጊዜያዊነት ስራ መስራት እንዴት ይታያል?

መልስ 15፡ ዲኑን ይፋ ማድረግ ያልቻለ ሙስሊም ከቻለ ወደሙስሊም አገር የመሰደድ

ግዴታ አለበት። ካልቻለ ግን አላህ መፍትሄ እስኪያመጣለት ድረስ የሚመጣበትን መከራ በትዕግስት ተሸክሞ በዲኑ ላይ ይጽና። በከሀዲዎች አገርም ይሁን በሌላ ዲኑን አጥብቆ መያዝ የግድ ነው።

ጥያቄ 16፡- የተለያዩ እምነት ተከታዮችና ስልጣኔ በሚል ርዕስ ሙስሊሞች ከከሀዲዎች ጋር የሚያደርጉት ውይይት እንዴት ይታያል?

መልስ 16፡- አላማው ከሙስሊሞች ያለውን መልካም ይፋ ለማድረግ ሌላው እምነት በስህተት ላይ መሆኑን ለማብራራትና ዳዕዋ ለማድረግ ክህደትን ትተው ወደኢስላም እንዲገቡ ጥሪ ለማድረግ ከሆነ ችግር የለውም። አላማው የሀይማኖቶች እኩልነትን ኢስላምን ከሌሎች የክህደት እምነቶች ጋር ለመቀላቀል ከሆነ ግን ውሸት የተሞላበት ውይይት በመሆኑ አይፈቀድም።

ጥያቄ 17፡- በሞባይል ቢዲዮ ህጻናቶችን መቅረጽ ሸሪዓዊ ብይኑ ምንድን ነው?


መልስ 17፡- በማንኛውም መልክ - በቪዲዩም ይሁን በሌላ - መቅረጽ አይፈቀድም። ረሡል ﷺ ሰዓሊያንን ረግመዋል። ረሡል ﷺ ሁሉም ሰዓሊያን የእሳት ናቸው ብለዋል። ስለዚህ የችግር ጊዜ ካልሆነ በቀር አይበቃም። የመቀረጽ ወይም ፎቶ የመነሳት ፍላጎት ሳይኖረው ለችግር ጊዜ ለምሳሌ ለመታወቂያ ፣ ለፓስፖርት ቢነሳ ይፈቀዳል። ለማስታወሻ ብሎ መነሳት ሀራም ነው።

ረሡል ﷺ የሚከተለውን ሐዲስ ተናግረዋል፡-

"لا تدخل الملائكة بيتا فيه كلب ولا صورة"

"ውሻ አና ቅርጻ ቅርጽ ያለበት ቤት መላኢካ አይገባም" *(ቡኻሪ፡ 3322, ሙስሊም፡ 2106)*

ፎቶን ከግድግዳ መስቀል ወደፊት የሽርክ ተግባር ለመፈጸም በር የሚከፍት በመሆኑ አደጋው የከበደ ነው።



ባህር ዳር በሚገኙ የአህሉሱና መሻይኾች የተቀሩ ጠቃሚ ኪታቦች፣ ከሀገር ውስጥና ከውጭ በሚመጡ መሻይኾች የተሰጡ ኮርሶች፣ ሙሐደራዎች፣ የጁመዓ ኹጥባ፣ በትክክለኛ ማስረጃ የተደገፉ የተለያዩ ኢስላማዊ መጣጥፎችን የሚከተለውን የቴሌግራም ኪንክ ጆይን በማድረግ መከታተል ይችላሉ



http://t.me/alateriqilhaq